በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው

ምስጋና ለአለማት ጌታ ለአላህ የተገባ ነው። የአላህ ሰላም እና እዝነት የነብያት መደምደሚያ በሆኑት መልዕክተኛዉ ሙሀመድ፣ በቤተሰቦቻቻውና በባልደረቦቻቸው ላይ ይስፈን። የአላህ መልእክተኛ ሳያብራሩልን ያለፉት ምንም አይነት ጉዳይ የለም። መልዕክታቸውን በሙሉ አድርሰው ሀላፊነታቸውን ተወጥተዋል።

ከዓብዳላህ ኢብን ዓምር ሙስሊም በዘገቡት ሀዲስ የተከበሩት የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ይላሉ:- **‹‹ለህዝቦቹ የሚያውቅላቸውን መልካም ነገር የሚያመለክታቸው ከሚያውቅላቸው መጥፎ ነገርም የሚያስጠነቅቃቸው ቢሆን እንጂ ከእኔ በፊት ማንም ነብይ አልተላከም››።** ሙስሊም ዘግበውታል

በነብያት እንደበት ከተብራሩት እውነታዎች ሁሉ ታላቁ **በአላህ አንድነት ማመንና ብቸኛ ተመላኪነቱን ማረጋገጥ ‹‹ተውሂድ›› ነዉ**። የተዉሂድን አጀንዳዎች ሙሉ በሙሉ በዚህች አጭር ዕሁፍ መዳሰስ ባይቻልም ጥቂት ከተዉሂድና ከሽርክ ጋር የተያያዙ ቁምነገሮችን በማብራራት የነብያትን በመልካም ነገር የማዘዝና ከክፉ ነገሮች የማስጠንቀቅ ፈለግ ለመከተል እንወዳለን።

ዓብዱላህ ኢብኑ መስዑድ እንዲህ ብለዋል:- የአላህን መልዕክተኛ **‹ከወንጀሎች ሁሉ የከፋው ወንጀል የትኛው ነው?›** ብዬ ጠየቅኳቸውና **‹አላህ ፈጥሮህ ሳለ ለርሱ አጋር ማድረግህ ነው› ሲሉ መለሱልኝ››** ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል

ይህ እንግዲህ ሽርክ ከወንጀሎች ሁሉ የከፋው ወንጀል መሆኑን ያሳያል። ሆኖም ግን በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የሽርክን ተግባር ብዙሀን የሚፈፅሙት ሆኖ እናገኘዋለን።

አላህ ብቸኛ በሆነባቸው እንደ ጌትነቱ፣ አምላክነቱ፣ ስሞቹና ባህሪያቶቹ ባሉ ጉዳዮች ላይ ሌሎችን ከእርሱ ጋር ማጋራት **ሽርክ** ይባላል። በአብዛኛው በማህበረሰባችን ውስጥ የሚታየው የሽርክ አይነት በአምላክነቱ ማለትም በአምልኮት ዘርፍ ላይ የሚፈፀመው ሆኖ እናገኘዋለን። ይህም የተለያዩ የአምልኮት አይነቶችን ከአላህ ውጪ ለሌሎች መፈፀምን ይመለከታል።

አምልኮ (ዒባዳ):-

ዒባዳ ማለት አላህ ለሚወዳቸው ውስጣዊም ሆነ ውጫዊ ንግግሮች እና ተግባሮች ሁሉ የተሰጠ ስያሜ ነው። የአምልኮ ዓይነቶች ብዙ ናቸው። ለምሳሌ:-

ለላት፣ ሩኩዕ፣ ሱጁድ፣ እርድ (የመቃረቢያ መስዋዕት)፣ ልመና (ዱዓእ)፣ መተናነስ (ኹሹእ)፣መመካት (ተወክል)፣ ፍራቻ (ኸዉፍ)፣ ተስፋ ማድረግ (ረጃዕ)፣ ጠዋፍ እና መሐላ እንዲሁም ሌሎች አላህ የደነገጋቸው የአምልኮ ዘርፎች ሁሉ ናቸው።

እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ለአላህ ብቻ የተገቡ የአምልኮ ተግባሮችን ከእርሱ ውጪ ላሉ አካላት ይጠቅሙናል ወይም ይጎዱናል፣ ወደ አምላካችን ያቃርቡናል በሚል በፊጣሪያችንና በአምላካችን በአላህ ላይ ማጋራት ሽርክ ነዉ።

ማጋራት ወይም ሽርክ በሁለት ይመደባል

አንደኛው “**አሽርክል-አክበር**” ወይም ታላቁ ሽርክ በመባል የሚታወቀው ሲሆን፣ ይህ የሽርክ ዓይነት ከፈጣሪ አምላካችን ከብቸኛው ጌታችን ከአላህ ውጪ ለፍጡራን ከላይ የተዘረዘሩ የአምልኮ ወይነቶችን መፈፀምን የሚመለከት ነዉ። የህንን ዓይነት ሽርክ የፈፀመ ግለሰብ ከኢስላም የሚያስወጣውን ተግባር ፈፅሟል።

ሁለተኛው “አሽርክል-አስገር” ወይም ታናሹ ሽርክ በመባል የሚታወቀው ሲሆን፣ ይህ የሽርክ ዓይነት ደግሞ ማንኛውንም በቀርአንና በሀዲስ ውስጥ “ሽርክ” የሚል ስያሜ የተሰጠውን ንግግር እና ተግባር የሚመለከት ነዉ። ወደ ታላቁ ሽርክ የሚያዳርስ ከመሆኑ አንፃር ከታላላቅ ወንጀሎች ሁሉ የከፋ ወንጀል ነው።ሆኖም ግን አንደ **“ትልቁ ሽርክ”** አንድን ግለሰብ ከኢስላም አያስወጣም።እንደ ምሳሌነትም አንድ ሰዉ አንድን መልካም ተግባር ለአላህ ሲል ብቻ መፈፀም ሲገባው ለሰዎች ውዳሴ (ይዩልኝና ይስሙልኝ) በሚል ከፈፀመው ትንሹን ሽርክ ፈፅሟል ይባላል። ይህ የሽርክ ዓይነት በቀጥታ ከኢስላም የሚያስወጣ ነው ባይባልም እንደ ዓይነቱና መጠኑ የሚመዘን ከፍም ዝቅም ሊል የሚችል ውሣኔ ያለው ከወንጀሎች ሁሉ የከፋ ነው።

የሽርክ አስከፊነትና የሚያስከትላቸዉ አደጋዎች

- **“አሽርኩል-አክበር”** ‹ታላቁ ሽርክ› ከኢስላም የሚያስወጣ ክህደት ነዉ።። አንድ ግለሰብ **ከአላህ በስተቀር አምልኮ የሚገባው እንደሌለ እመስክራለሁ** ካለ ሙስሊምነቱ የተረጋገጠ ነው። ሆኖም ይህንን እምነቱን እና የምስክርነት ቃሉን የሚያፈርስ የባዕድ አምልኮ **ሽርክ** ከፈፀመ ምስክርነቱን አፍርሷል፣ ከኢስላምም ወጥቷል።

- ትልቁ ሽርክ የአንድን ግለሰብ መልካም ስራዎች ሙሉ በሙሉ ያበላሻል።

አላህ በሱረቱል አንዓም በሚገኙ አንቀጾች ላይ እንደ ነብየላሂ ኢብራሂም፣ኢስሀቅ፣ኑህ፣ሙሳ፣ኢሳ ያሉ አስራ ስምንት ነብያትን ስም ከጠቀሰ በኋላ እንዲህ ይላል:-

﴿وَلَوْ أَشْرَكُوا۟ لَحَبِطَ عَنْهُم مَّا كَانُوا۟ يَعْمَلُونَ ﴿٨٨﴾﴾ الأنعام: ٨٨

‹‹ ባጋሩም ኖሮ ይሠሩት የነበሩት ስራ በታበሰ ነበር›› አል አንዓም 88

የነብያት መደምደሚያና የሰው ልጆች አለቃ ለሆኑትም የአላህ መልዕተኛ ሙሀመድ አንዲህ በማለት ነግሯቸዋል

﴿لَئِنْ أَشْرَكْتَ لَيَحْبَطَنَّ عَمَلُكَ وَلَتَكُونَنَّ مِنَ الْخَٰسِرِينَ ﴿٦٥﴾﴾ الزمر: ٦٥

‹‹ብታጋራ ስራህ በእርግጥ ይታበሳል፣ በእርግጥም ከከሐዲዎች (ከከሰሩት) ትሆናለህ...››› አል ዙመር 65

- ታላቁ ሽርክ ለአንድ ግለሰብ ፈፅሞ ጀነት አለመግባት ሰበብ ከመሆኑም ባሻገር ዝንተለለም በእሳት ውስጥ ዘውታሪ እንዲሆን ምክንያት የሚሆን ወንጀል ነው። አላህ በነብዩላህ ኢሳ አማካኝነት ያስተላለፈውን መልዕክት አስመልክቶ እንዲህ በማለት ይገልፅልናል

﴿إِنَّهُۥ مَن يُشْرِكْ بِٱللَّهِ فَقَدْ حَرَّمَ ٱللَّهُ عَلَيْهِ ٱلْجَنَّةَ وَمَأْوَىٰهُ ٱلنَّارُ ۖ وَمَا لِلظَّٰلِمِينَ مِنْ أَنصَارٍ ﴿٧٢﴾﴾ المائدة: ٧٢

‹‹እነሆ! በአላህ የሚያጋራ ሰው አላህ በርሱ ላይ ጀነትን በእርግጥ እርም አደረገ፣ መኖሪያውም እሳት ናት፣ ለበዳዮችም (ለአጋሪዎችም) ምንም ረዳቶች የሏቸውም›› አል ማዒዳህ 72

ጃቢር ኢብኑ ዓብዲላህ ባስተላለፉት ሀዲስ ላይ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል **‹‹አላህህ ጋር ማንንም ምንንም ሳያጋራ የሞተ ሰው ጀነት ገባ፣ ከአላህ ጋር ሌላን እያጋራ የሞተ ሰው እሳት ገባ›››** ሙስሊም ዘግበውታል

- **ተውሂድ** ፈጣሪ አላህን አምልኮት የሚገበው እርሱ ብቻ ስለሆነ አምልኮትን ለርሱ ብቻ በማድረግ የሚፈፀም ፍትህ እንደሆነ ሁሉ **ሽርክም** አምልኮትን አምላክና ፈጣሪ ከሆነው አላህ ውጪ ለሌላ አካል በማዋል የሚፈፀም **ከበደሎች ሁሉ የከፋ በደል** ነው።

አላህ ሉቅማን ለልጁ ያስተላለፈውን መልዕክት አስመልክቶ እንዲህ ይላል:-

﴿ وَإِذْ قَالَ لُقْمَٰنُ لِٱبْنِهِۦ وَهُوَ يَعِظُهُۥ يَٰبُنَىَّ لَا تُشْرِكْ بِٱللَّهِ ۖ إِنَّ ٱلشِّرْكَ لَظُلْمٌ عَظِيمٌ ﴿١٣﴾﴾ لقمان: ١٣

“ **‹‹ሉቅማንም ለልጁ እርሱ የሚገስፀው ሲሆን ፣ ልጄ ሆይ! በአላህ አታጋራ ማጋራት ታላቅ በደል ነውና.... ያለውን (አስታውስ))››** ሱረቱ ሉቅማን 13

ከዚህ በላይ በሰፈረዉ ዕሁፍ ከወንጀሎች ሁሉ የከበደዉን ወንጀል የሽርክን አስከፊነት ተመልክተናል በመቀጠልም በማህበረሰበባችን ውስጥ እየተንፀባረቁ ካሉ ገፅታዎቹ ጥቂቶቹን ለመጠቆም እሞክራለሁ::

ፍጡራንን መማፀንና ዱዓን ለእነርሱ ማቅረብ

አላህ እንጂ ሌላ ማንም በማይችለው ጉዳይ ላይ ከአላህ ሌላ የሆነን አካል መለመን፣እርዳታን እና ጥበቃን መጠየቅ እንዲሁም ድረሱልኝ ማለት ... እነዚህ የተለያዩ የ ‹‹ዱዓዕ›› ወይም ‹‹ዐለት›› ክፍሎች ናቸው። ኑዕማን ኢብኑ በሺር ባስተላለፉት ሀዲስ የአላህ መልዕክተኛ ‹‹ዱዓዕ›› ለአላህ ብቻ የሚገባ አምልኮ መሆኑን እንዲህ በማለት ይገልፁልናል:-

‹‹(ዱዓእ) እርሱ እራሱ አምልኮ ነው።››› (ኢማሙ አህመድ፣ ቲርሚዚይ እና ሌሎችም ዘግበውታል)

☛ **‹‹ሽርክ››** ማለት ለአላህ ብቻ የሚገባን ‹ዒባዳ› ወይም አምልኮ ለሌላ አላልፎ መስጠት ነው። ስለሆነም ከላይ የጠቀስናቸውን የተለያዩ የዱዓእ ክፍሎች ለነብያት፣ ለመላኢክት (ለመላእክት)፣ ለጂኖች (ለአጋንንት)፣ ለሞቱም ሆነ በህይወት ላሉ ደጋግ የአላህ ባሮች (ሷሊሆች)፣ ለአላህ ወዳጆች (ወልዮች) ... ወዘተ ማዋል ከታላቁ ሽርክ ውስጥ የሚመደብ ተግባር ነው። ፍጡራንን ‹‹ያ ረሱለላህ! ያ ዐሊይ! ያ ሰይዳ ፋጢማ! ያ ሁሰይን! ያ አብዱልቃድር ጀይላኒ! ያ ሰይዳ ዘይነብ! ያ ነጃሺ! ያ ኑርሁሰይን! ያ አብራሽ! ያ ቃጥባሬ! ያ አልከስዩ! ያ ሐጂ አሊዬ! ... ወዘተ እያሉ አላህ እንጂ ሌላ ማንም ሊፈፅመዉ በማይችለው ጉዳይ ላይ ለምሳሌ:- ‹‹ልጅ የለኝምና ልጅ ስጡኝ››፣ ‹‹ታምሜያለሁና ፈውሱኝ››፣ ‹‹ተርቤያለሁና ሲሳይን ለግሱኝ››፣ ‹‹ተጨንቄያለሁና ከጭንቅ አውጡኝ››፣ ‹‹ፈርቼያለሁ እና ከአደጋ ጠብቁኝ››፣ ‹‹ከጀሀነም እሳት ጠብቁኝ››፣ ‹‹ለጀነት አብቁኝ››፣ ‹‹አማላጅ ጠበቃ ሁኑኝ›› በማለት እነሱን መጥራትና መማፀን እና ድረሱልኝ ማለት በጥብቅ የተከለከለ ግልፅ የሽርክ ተግባር ነው።

Ø ይህ አይነቱ ጥሪ ሽርክ መሆኑን ከሚያመላክቱ እጅግ በጣም በርካታ የቁርዓን እና የሀዲስ መረጃዎች መካከል ጥቂቶቹን ብቻ ለመጠቆም እሞክራለሁ።

አላህ እርሱ እንጂ ሌላ ማንም በማይችለው ጉዳይ ላይ ሌላን እርዳታ እንዳንጠይቅ ቃል ሲያስገባን እንዲህ ይላል።

﴿إِيَّاكَ نَعْبُدُ وَإِيَّاكَ نَسْتَعِينُ ﴿٥﴾﴾ الفاتحة: ١ - ٥

‹‹አንተን ብቻ እናመልካለን፣አንተንም ብቻ እርዳታ እንለምናለን›› አል-ፋቲሀ5

☛ እንዲሁም አላህ የሰው ልጆች ከደጋሚ፣ ከመተተኛ እና ከጠንቋይ፣ ከኢጋንንት እና ከሌሎች እርኩሳን አካላት ክፋት እና ሴራ በእርሱ ብቻ እንዲጠበቁ ያዘዉ

አላህ መልዕክተኛዉን እንዲህ እንዲሉ አዟቸዋል።

﴿قُلْ أَعُوذُ بِرَبِّ ٱلْفَلَقِ ﴿١﴾ مِن شَرِّ مَا خَلَقَ ﴿٢﴾ وَمِن شَرِّ غَاسِقٍ إِذَا وَقَبَ ﴿٣﴾ وَمِن شَرِّ ٱلنَّفَّٰثَٰتِ فِى ٱلْعُقَدِ ﴿٤﴾ وَمِن شَرِّ حَاسِدٍ إِذَا حَسَدَ ﴿٥﴾﴾ الفلق: ١ - ٥

‹‹ካፈጠረው ፍጡር ሁሉ ክፋት፣ ከሌሊት ክፋት ባጨለመ ጊዜ፣ የተቋጠሩ (ክሮች) ላይ ተፊዎች ከሸኑት(መተተኛ) ሴቶችም ክፋት፣ ከምቀኛም ክፋት በተመቀኘ ጊዜ በተፈልቃቂው ጎህ ጌታ እጠበቃለሁ›› አል- ፈለቅ 1-5

አላህ ብቻ እንጂ ሌላ ማንም በማይችለው ጉዳይ ላይ አንድ ሰዉ ከችግር እንዲያወጣውም ይሁን ጥቅምን እንዲያስገኝለት ሌላን አካል ድረስልኝ ብሎ መማፀኑ ችግሩን እንዳማያስወግድለት ወይም ጉዳቱን እንደማይመክትለት ከመግለፅም ባሻገር ይህ ተግባርና እምነት ክህደት እንደሆነ ተናገሯል።

﴿ وَمَنْ أَضَلُّ مِمَّن يَدْعُوا۟ مِن دُونِ ٱللَّهِ مَن لَّا يَسْتَجِيبُ لَهُۥٓ إِلَىٰ يَوْمِ ٱلْقِيَٰمَةِ وَهُمْ عَن دُعَآئِهِمْ غَٰفِلُونَ ﴿٥﴾ وَإِذَا حُشِرَ ٱلنَّاسُ كَانُوا۟ لَهُمْ أَعْدَآءً وَكَانُوا۟ بِعِبَادَتِهِمْ كَٰفِرِينَ ﴿٦﴾﴾ الأحقاف: ٥ - ٦

‹‹ከአላህ ሌላ እስከ ትንሳኤ ቀን ድረስም ለእርሱ የማይመልስለትን (ፍጡር) ከሚለምን ሰው ይበልጥ ጃኅሳላት ማንነው? እነርሱም ከጥሪያቸው ዘንጊዎች ናቸው። ሠዎችም (በተቀሰቀሱና) በተሰበሰቡ ጊዜ (ለማልክቱ) የእነርሱ ጠላት ይሆናሉ። (እነርሱንም) ማምለካቸውን ከሀዲዎች ይሆናሉ።››› ሱረቱል አህቃፍ 5-6

ዓብዱላህ ኢብኑ መስዑድ ባስተላለፉት ሀዲስ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ይላሉ ‹‹ **ከአላህ ዉጭ ሌላን አካል ለአላህ አጋር አድርጎ መለመንን ሳይተዉ (ተውበት ሳያደርግ) የሞተ ሰው እሳት ገባ››** ቡኻሪ ዘግበውታል

በሌላ ሀዲስም የአላህም መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል **‹‹መለመንን ስትፈልግ አላህን ብቻ ለምን፣ እርዳታንም ብትፈልግ በአላህ ብቻ ተረዳ››** ቲርሚዚይ ዘግበውታል

ለፍጡራን ሥለትን መሳል

በማህበረሰባችን ውስጥ ከሚንፀባረቁት የሽርክ አይነቶች አንዱ ዑለማዎች ከታላቁ የሽርክ አይነት የሚመድቡት ሥለትን ከአላህ ሌላ ላለ አካል ማድረስ ነው። ስለት ማለት አንድ ሰው በእርሱ ላይ ግዴታ ያልሆነበትን ነገር በራስ ተነሳሽነት እራሱ ላይ ግዴታ ማድረጉ ነው። ይህ ደግሞ ከአላህ በቀር ለማንም የማይፈፀም **አምልኮ** መሆኑን የሚጠቁሙ የቁርዓንና የሀዲስ መረጃዎች ብዙ ናቸው።

አላህ በሱረቱል ሀጅ እንዲህ ይላል:-

﴿وَلْيُوفُوا۟ نُذُورَهُمْ﴾ الحج: ٢٩

‹‹ ስለቶቻቸውንም ይሙሉ...›› አል ሀጅ 29

በሌላውም የቁርዓን አንቀፅ አላህ ደጋግ የሆኑ ባሮቹን ባህሪ ሲገልፅ እንዲህ ይላል:-

﴿يُوفُونَ بِٱلنَّذْرِ وَيَخَافُونَ يَوْمًا كَانَ شَرُّهُۥ مُسْتَطِيرًا ﴿٧﴾﴾ الإنسان: ٧

‹‹ ስለቶቻቸውን ይሞላሉ፣መከራዉ ተሰራጭ የሆነንም ቀን ይፈራሉ ›› አል-ኢንሳን 7

እናታችን ዓኢሻ ባስተላለፉት ሀዲስ ላይ የአላህም መልዕክተኛ እንዲህ ይላሉ:-

‹‹አላህን ለመታዘዝ (የአላህን ህግ ለመተግበር) የተሳለ ሰው ስለቱን ያሟላ፣ በአላህ ላይ ለማመፅ (የአላህን ህግ ለመጣስ) የተሳለ ሰው ግን እንዳይፈጥስ›› ቡኻሪ ዘግበውታል

☛ እነዚህ የቁርዓን የሀዲስ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ስለት ከአምልኮት አይነቶች መካከል አንዱ ነዉ። በተለይ በመጀመሪያው አንቀፅ ላይ ስለትን መሙላት ግዴታ መሆኑን በሚያነሳ መልኩ አላህ ካዘዘ ዒባዳ መሆኑን ያመለክታል።

አንድን የአምልኮ ክፍል ቅንጣት ታህል እንኩ ከአላህ ሌላ ላለ አካል መስጠት ‹‹ሽርክ›› ነው። ስለዚህም ስለትን ከአላህ ሌላ ለፍጡራን ማድረስ ከኢስላም የሚያስወጣ የሽርክ ተግባር ነው።

ለደጋግ የአላህ ባሮች ፣ለመላዕክት፣ ለሙታኖች፣ ለጂኖችና ለመሳሰሉት መላል ግልፅ የሆነ የሽርክ ተግባር ነዉ።

ለፍጡራን ማረድ

ከታላቁ የሽርክ አይነት አንዱ ከአላህ ሌላ ለነብያት፣ ለጂኖች(አጋንንት)፣ ለተለያዩ ጣኦታት፣አድባራት፣ ወልዮች... ማረድ ነው። እርድን ለአላህ ብቻ በማድረግ ወደ አላህ መቃረብ እንደሚገባ፣ በአንባሩም ከአላህ ሌላ ላለ ለማንኛዉም አካል ማረድ ሽርክ መሆኑን የሚያስረዱ የቁርዓንና የሀዲስ መረጃዎች ብዙ ናቸዉ። ይህም፣ እርድ ከዚህ በፊት እንዳየናቸዉ የሽርክ አይነቶች ሁሉ ለአላህ ብቻ የሚገባውን አምልክ ለሌላ መስጠት በመሆኑ ነው። ከመረጃዎቹም መካከል የተወሰኑት እንደሚከተሉት ይነበባሉ፦

﴿ قُلْ إِنَّ صَلَاتِي وَنُسُكِي وَمَحْيَايَ وَمَمَاتِي لِلَّهِ رَبِّ الْعَالَمِينَ ﴿١٦٢﴾ لَا شَرِيكَ لَهُ ۖ وَبِذَٰلِكَ أُمِرْتُ وَأَنَا أَوَّلُ الْمُسْلِمِينَ ﴿١٦٣﴾ ﴾

الأنعام: ١٦٢ - ١٦٣

‹‹ሰግደቴ፣ እርዱም፣ ሕይወቴም፣ ሞቴም ለዓለማት ጌታ ለአላህ ነው በል። ለርሱ ተጋሪ የለውም በዚህም (አላህን በማጥራት) ታዘዝኩ›› አል አንዓም 162-163

በሌላውም የቁርዓን አንቀጽ አላህ(ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፦

﴿ إِنَّا أَعْطَيْنَاكَ الْكَوْثَرَ ﴿١﴾ فَصَلِّ لِرَبِّكَ وَانْحَرْ ﴿٢﴾ ﴾ الكوثر: ١ - ٢

‹‹እኛ በጣም ብዙ በጎ ነገሮችን ሰጠንህ፣ ስለዚህ ለጌታህ ስገድ፣ ለርሱም (በስሙም) እረድ›› አል-ከውሰር 1-2

ዓሊይ ኢብኑ አቢጣሊብ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፦

‹‹ከአላህ ሌላ ላለ አካል ያረደን ሰው አላህ ከእዝነቱ ያርቀው›› ሙስሊም ዘግበውታል

ይህ ሲባል ወደ እነሱ ለመቃረብ ሲባል ማረድ ማለት ነዉ እንጂ በነርሱ ስም ማረድ ማለት አይደለም። በነርሱ ስም የታረደ ከሆነ በወንጀሉ ላይ ወንጀል በክህደት ላይ ሌላ ክህደት ነው የሚሆነው።

ከአደጋ ለመጠበቅ የሚንጠለጠሉና የሚጠለቁ ነገሮች

በብዙ ማህበረሰቦች ዉስጥ ከተዛመቱ አደገኛ የሽርክ ተግባሮች መካከል በሰዎች፣ በእንስሳት፣ በቤቶችና በመኪኖች ላይ የቡዳ (የአይነናስ) እና ከማንኛዉም አደጋ የጠብቃል፣ ገበያን ያደራል፣ ጥሩ አድል ያስገኛል ...ወዘተ በሚል የሚንጠለጠሉና የሚታሰሩ የሚጠለቁ ነገሮች ሁሉ እዚህ የሽርክ አይነት ዉስጥ ይካተታሉ። ይህንን በተመለከተ ከዐቅባህ ኢብኑ ዓሚር በተላለፈው ሀዲስ ላይ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ይላሉ፦ **‹‹ኸረዝ›› (እርዝ በመባል የሚታወቀውን) ያንጠለጠለ ሰው ጉዳዩን አላህ አያሟላለት፣ ‹‹ወደዓ›› (እንደ ዛጎል ያለን) ያንጠለጠለ ሰው አላህ እረፍት አይስጠው››** በሌላ ዘገባም እንዲህ ብለዋል፣ **‹‹ኸረዝን (እንደ እርዝ ያለን) ያንጠለጠለ ሰው በአላህ ላይ በእርግጥ አጋርቷል››**

የሁሉንም ሀዲሶች ኢማሙ አህመድና ሀኪም ዘግባዋቸዋል። ሆኖም ይህ ከሚንጠለጠሉ ነገሮች ጋር የተያያዘው የሽርክ አይነት ከኢስላም ከሚያስወጣዉ ታላቁ ሽርክ ዉስጥ የሚካተተው አንጠልጣዩ ወይም አጥላቂው ግለሰብ በዚህ ነገር ላይ ካለው እምነት እንዳር ነው። ይህም ማለት፣ ይህ ሰዉ ‹ያንጠለጠለዉ› ያሰረዉ ወይም ያጠለቀዉ ገመድና መሰል ነገር በራሱ ጥቅምን ያመጣልኛል ወይም ከጉዳት ይጠብቀኛል ብሎ ከሆነ **ታላቁ ሽርክ ውስጥ የሚካተት** ሲሆን፣ ነገር ግን እንደምክንያት ወይም ሰበብ ይሆናል በሚል ከሆነ ከ ትንሹ የሽርክ አይነት የሚመደብ ይሆናል። ትልቁም ይሁን ትንሹ ሽርክ አደጋዉ የከበደ፣ የአላህም ዛቻ የበረታበት፣ ከወንጀሎች ሁሉ የከበደ በመሆኑ ከሁሉቱም የሽርክ አይነቶች መራቅ የግድ ይላል።

ምልጃና የመሸሪኮች ብዥታ

እዚህ ላይ ሳይጠቀስ የማይታለፈው ጉዳይ፣ ብዙዉን ጊዜ ከአላህ ሌላ ወልዮች ናቸው ብለው የሚያስቧቸውን ሰዎች የሚማፀኑ ለእነርሱም ሌሎች የአምልክ ተግባራትን የሚያዉሉ ሰዎች ከጥንት ጀምሮ ለስራቸዉ ህጋዊነት እንደ መረጃ የሚጠቅሱት የሸፈዓ(ምልጃ) ጉዳይ ነዉ።

እንዲህም ይላሉ፦ *‹‹እኛ እነዚህን አካላት ስንለምናቸው፣ ድረሱልን፣ ጠብቁን ስንላቸው እንዲሁም እርድንና ስለትን ለነርሱ ስናደርግ እነርሱን ማምለካችን ሳይሆን እኛ ወንጀለኞች ስለሆንን እነርሱ ደግሞ ሷሊህ ደግ የአላህ ባሮች ስለሆኑ ወደ አላህ እንዲያቃርቡን ሸፈዓ እንዲሆኑን ብለን ነው››*። ለዚህ ብዥታቸዉ በብዙ ዑለማዎች ዝርዝር ምላሽ ተሰጥቷል። ጥቅል ምላሽ ለመስጠት፦

☛ ሸፈዓ(ምልጃ) ሁሉም የአላህ ነዉና ከእርሱ ብቻ ነዉ የሚለመነዉ። አላህ እንዲህ ይላል፦

﴿ قُل لِّلَّهِ الشَّفَاعَةُ جَمِيعًا ﴾ الزمر: ٤٤

‹‹ምልጃ መላዉም የአላህ ብቻ ነዉ››› ዙመር 4

አላህ በተለያዩ አንቀፆች የምልጃን መስፈርቶች ጠቅሷል።

- አማላጁ የአላህን ፍቃድ ማግኘት ይኖርበታል ::በዚህም አላህ ክብርን ይለግሰዋል።

﴿ مَن ذَا الَّذِي يَشْفَعُ عِندَهُ إِلَّا بِإِذْنِهِ ﴾ البقرة: ٢٥٥

‹‹ያ እርሱ ዘንድ በእርሱ ፍቃድ ቢሆን እንጂ የሚያማልድ ማነዉ? (ማንም የለም)›› አል-በቀራህ 255

- ከምልጃ ተጠቃሚ መሆን የሚችለዉ አላህ የፈቀደለት እና ንግግሩን የወደደለት ብቻ ነዉ።

﴿ يَوْمَئِذٍ لَّا تَنفَعُ الشَّفَاعَةُ إِلَّا مَنْ أَذِنَ لَهُ الرَّحْمَٰنُ وَرَضِيَ لَهُ قَوْلًا ﴿١٠٩﴾ ﴾ طه: ١٠٩

‹‹በዚያ ቀን ለእርሱ አል-ረህማን የፈቀደለትና ቃሉንም የወደደለትን ሰዉ ቢሆን እንጂ ምልጃ (አንድንም) አትጠቅምም›› ጣሀ 109

- ከምልጃ ተጠቃሚ መሆን የሚችለዉ አላህን በብቸኝነት የሚያመልክና ከሽርክ የራቀ ሙወሂድ ብቻ ነዉ።

﴿ وَلَا يَمْلِكُ الَّذِينَ يَدْعُونَ مِن دُونِهِ الشَّفَاعَةَ إِلَّا مَن شَهِدَ بِالْحَقِّ وَهُمْ يَعْلَمُونَ ﴿٨٦﴾ ﴾ الزخرف: ٨٦

‹‹እነዚያም ከአላህ ሌላ የሚያመልኳቸዉ አነርሱ የሚያዉቁ ሆነዉ በእዉነት(አላህ በቀር በእዉነት የሚመለክ አንደሌለ) ከመሰከሩት በስተቀር ምልጃን አይችሉም›› ዙኽሩፍ 86

አቡ ሁረይራ ነብዩን ‹በእርስዎ ሸፋዓ በጣም ተጠቃሚ የሚሆነዉ ማን ነዉ? በማለት ሲጠይቃቸዉ ‹ከልቡ በኢኽላስ ላ ኢላህ ኢለላህ ያለ ሰዉ› በማለት መለሱለት። (ቡኻሪ ዘግበዉታል)

በአላህ የሚያሻርክ ምልጃ ሊጠቅመዉ አይችልም። የምልጃ ተጠቃሚ የሚያደርገዉ ተዉሂድ ነዉ። ታዲያ እንዴት ሽርክን በመፈፀም የምልጃ ተጠቃሚ ለመሆን ትሞክራላችሁ?

☛ አንድ የአምልኮ ተግባር (ዒባዳ) በማንኛዉም ሁኔታ ከአላህ ሌላ ላለ አካል ሊፈፀም አይገባም ለፍጡር ከተሰጠ ግን ያ አካል ለአላህ አጋር ተደርጎ ተይዟል ማለት ነዉ። ስለዚህ ለእነርሱ የምትፈፅሙት አምልኮ የሽርክ ተግባር ነዉ።

☛ ይህ አይነቱ ምክንያት በመካ የነበሩ ሙሽሪኮች (አጋሪዎች) ለመልዕክተኛው ሲሰጡት የነበሩት የተለመደ ምላሽ ነው። ሆኖም ግን ይህ ምላሻቸዉ ለእነርሱ የተሰጣቸዉን የሙሽሪክነት ብይን አልቀየረዉም። አላህ ይህንን እውነታ በማስመልከት እንዲህ ይላል፦

﴿ وَالَّذِينَ اتَّخَذُوا مِن دُونِهِ أَوْلِيَاءَ مَا نَعْبُدُهُمْ إِلَّا لِيُقَرِّبُونَا إِلَى اللَّهِ زُلْفَىٰ إِنَّ اللَّهَ يَحْكُمُ بَيْنَهُمْ فِي مَا هُمْ فِيهِ يَخْتَلِفُونَ ۗ إِنَّ اللَّهَ لَا يَهْدِي مَنْ هُوَ كَاذِبٌ كَفَّارٌ ﴿٣﴾ ﴾ الزمر: ٣

‹‹እነዚያም ከርሱ ሌላ (አማልክትን) ረዳቶች አድርገዉ የያዙት ‹ወደ አላህ ማቃረብን እንዲያቃርቡን እንጅ ለሌላ አናመልካቸውም› ይላሉ። አላህ እርሱ ውሽታም ከሀዲ የሆነን አያቀናም›› አል-ዙመር 3

በሌላም አንቀፅ አላህ እንዲህ ይላል፦

﴿ وَيَعْبُدُونَ مِن دُونِ اللَّهِ مَا لَا يَضُرُّهُمْ وَلَا يَنفَعُهُمْ وَيَقُولُونَ هَٰؤُلَاءِ شُفَعَاؤُنَا عِندَ اللَّهِ ۚ قُلْ أَتُنَبِّئُونَ اللَّهَ بِمَا لَا يَعْلَمُ فِي السَّمَاوَاتِ وَلَا فِي الْأَرْضِ ۚ سُبْحَانَهُ وَتَعَالَىٰ عَمَّا يُشْرِكُونَ ﴿١٨﴾ ﴾ يونس: ١٨

‹‹ ከአላህም ሌላ የማይጎዳቸውን የማይጠቅማቸዉንም ያመልካሉ። **‹እነዚህም አላህ ዘንድ አማላጆቻችን ናቸው›** ይላሉ። በሰማያትና በምድር ውስጥ የማያውቀው ነገር ናሮ አላህን ትነግሩታላችሁን? በላቸው፤ (አላህ) ከሚያጋሩት ሁሉ ጠራ! ላቀም›› ዩኑስ 18

ይህ የሙሽሪኮች ምክኒያት መሆኑ ከታወቀ ከነሱ መንገድና እምነት መራቅ ግዴታችሁ ነዉ።

ሌሎችም ከተዉሂድና ከሽርክ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ብዙ ነጥቦች አሉ። አያንዳንዱ ሙስሊም እምነቱን ከአፍራሽ ነገሮች ይጠብቅ ዘንድ ሊያዉቃቸዉ ይገባል። ለዚህ ደግሞ ተዉሂድን የሚያብራሩ መሠረቶችን መማሩ ወሳኝ ነዉ። አላህ እምነታችንን ከሽርክ ጠብቀን፣ እዉነተኛ ተዉሂድ ላይ የምንሞት ያድርገን።

‹‹አላህ ሆይ! እያወቅኩ አንዳችን ከአንተ ጋር ከማሻረክ በአንተ እጠበቃለሁ፤ ለማላውቀውም ከአንተ ምህረት እጠይቃለሁ››

ኢማሙ ሀኪም የዘገቡት

ነሲሀ ተከታታይ ኢስላማዊ መልዕክት ቁ.4
www.nesiha.net

እምነትህን ጠብቅ

ዝግጅት
አቡ ዓብዱልሙሀይሚን

﴿ إِنَّهُ مَن يُشْرِكْ بِاللَّهِ فَقَدْ حَرَّمَ اللَّهُ عَلَيْهِ الْجَنَّةَ وَمَأْوَاهُ النَّارُ ۖ وَمَا لِلظَّالِمِينَ مِنْ أَنصَارٍ ﴿٧٢﴾ ﴾ المائدة: ٧٢

‹‹እነሆ! በአላህ የሚያጋራ ሰው አላህ በርሱ ላይ ጀነትን በእርግጥ እርም አደረገ፤ መኖሪያውም እሳት ናት፤ ለበዳዮችም (ለአጋሪዎችም) ምንም ረዳቶች የሏቸውም›› አል ማዒዳህ 72

ናጂያ ኢስላማዊ ማህበር
☎ +2511112758398
fax +2511112758399 ✉ 50151
Addis Ababa, Ethiopia

future graphic design